**ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ**
Kinijit Ethiopian Cultural and Relief Organization in Toronto
998 Bloor St West,, P.O.Box 10666, Toronto, ON  M6H - 1L8
**Tel./ Fax:  416 - 516 1244**

# <u>ግልጽ ደብዳቤ</u>

ለክብርት ወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ
አሜሪካን አገር ባሉበት
ለተከበሩ ዶክተር ኃይሉ አርአያ
አሜሪካን አገር ባሉበት
ለተከበሩ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው
አሜሪካን አገር ባሉበት
ለተከበሩ አቶ ብሩክ ከበደ
አሜሪካን አገር ባሉበት
ለተከበሩ ደክተር ብርሃኑ ነጋ
አሜሪካን አገር ባሉበት

ክብርትና ክቡራን፣

እንደሚታወሰው ሁሉ ነሐሴ 12 ቀን 1999 ዓ ም ወደ ካናዳ ስለሚመጣው የልዑካን ቡድንን አስመልክቶ ለክብርት ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ደብዳቤ ጽፈን ነበር፡፡ ወደ ካናዳ ልዑካን እንልካለን ስትሉ ጉዳዩ የሚመለከተው በቀጥታ እኛን ቢሆንም አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ መልስ ሳትሰጡን ወደ አሜሪካ መጣችሁ፡፡ ለማስረጃም ያህል የዚያን ደብዳቤ ትክክለኛ ግልባጭ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን አቅርበናል፡፡

ክቡር ኢጂነር ኃይሉ ሻውል ቪዛ አግኝተው መስከረም 4 ቀን 2000 ዋሽንግተን ዲሲ ሲገቡ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ በአውሮፕላን ማረፊያ ተገኝቶ ከፍ ያለ አቀባበል ሲያደርግላቸው "ገለልተኛ" ተብሎ የተቋቋመውም አስተናጋጅ ቡድን ይሁን እናንተም በቦታው ተገኝታችሁ አልተቀበላችኋቸውም፡፡ ድርጊቱ በጣም ገርሞናል፣ አሳዝኖናልም፡፡

ውሎ አድሮም ከእርሳቸው ጋር በመሆንና በመመካከር የመጣችሁበትን ጉዳይ ታከናውናላችሁ ብለን ስንጠባበቅ እናንተ ግን እርሳቸውን በማግለል በየሄዳችሁበት ከተማ ሁሉ የልዑካን ቡድኑ ወደ አሜሪካ ሲመጣ ሊያከናውን የሚገባውን ሥራ ሳይሆን የራሳችሁን ቡድን አጀንዳ በማካሄድ ላይ ከረማችሁ፡፡

ለረጂም ጊዜ ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩ የድጋፍ ድርጅቶች እንደሌሉ በመቁጠር በእነርሱ ላይ በተለጣፊነት የተቂቂሙትን ብቻ በመገናኘትና እውቅና በመስጠት መጓዛችሁ ወገንተኛነትን የሚያሳይ እንጂ ከእናንተ አመራር ቦታ ላይ ካላችሁ የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ይህም በመፍትሔ ፈንታ የበለጠ ማለያየት እንደያዛችሁ ዓለም በሙሉ ሊያየው በመቻሉ ፍርዱን ለሕዝብ እንተወዋለን፡፡ በውጭ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታትና የተጣሉትን ለማስታረቅ ነው የምንሄደው ያላችሁት ሁሉ ከንቱ ወሬ ሆኖ በመቅረቱ በእጅጉ አሳዝኖናል፡፡

በአሜሪካ በየትኛውም ከተማ ሁለቱንም ወገን ለማነጋገር ከቶም የሞከራችሁበት ሥፍራ የለም፡፡ እንዲያውም በእናንተ ወገንተኛነት የተነሳ የበለጠ ለመለያየትና ለመከፋፈል ምክንያት በመሆናችሁ፣ ይህንን ከፋፋይ ድርጊትና ከመሪያችሁ ተነጥላችሁ መጓዛችሁን በማውገዝ ብዙ የድጋፍ ድርጅቶች የተቃውሞ መግለጫ አውጥተውባችኋል፡፡ ለምሳሌ በሲያትል ቀድሞ የነበረው የድጋፍ ድርጅት ሳይሆን ከድጋፍ ድርጅቱ ውጭ የተመረጡ ሰዎች ዝግጅቱንና ስብሰባውን እንዲያዘጋጁ መደረጉ በጣም የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ድርጊት ነው፡፡

በውጭ የሚኖረው ደጋፊና አገር ወዳጁ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በጊዜው፣ በጉልበቱና በገንዘቡ ሲያደርግ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ልፋት ሁሉ መና አስቀርቶ ከአንድ ቡድን ጋር መጋዛችሁ፤ መሪዎቻችን፤ መሪዎቻችን ያላልናችሁን ያህል በዚህ ድርጊታችሁ በጣም አዝነናል፤ አፍረንባችኋል፤ ተቆጥተናልም።

ተግባራችሁና የያዛችሁትም አጀንዳ ቅንጅትን ለመከፋፈልና ለማዳከም ብሎም በጣም ብዙ ሕዝብ (ሴት ፣ ወንድ ፣ሕጻን ፣ ወጣት፣ ሽማግሌ ጨምሮ) ሕይወቱን የሰጠበትን፣ በሺህ የሚቆጠር የታሰረበትን፣ የተደበደበበትንና የተሰደደበትን ፣ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የት እንደደረሱ የማይታወቅበትን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከፍተኛ ትግል መና የሚያስቀር በመሆኑ እጅጉን አስቆጥቶናል።

የኛ ትግልና አጀንዳ ያልተከፋፈለና የተጠናከረ ቅንጅትን ይዘን የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የወሰነውን ውሳኔ ማስከበር ነው። ውሳኔው የሚከበረው ስምንቱ ከወያኔ ጋር መደራደሪያ ነጥቦች በሕጋዊ ውይይት ከሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ነው። ይህ ሳይሆን ወደፊት መሄድ አይቻልም። ይህንን አቋም የወያኔ ነፍስ አባቶችና የወያኔ ምንደኞችና ተላላኪዎች የአክራሪዎች አቋም ነው እያሉ ሊያጣጥሉት ይፈልጋሉ። በመሪያችንና እኛ ላይ አስጸያፊ አርማ ሊለጥፉ የሚሞክሩት ስም የሚወጣው በተግባር እንጂ በአሉባልታ እንዳልሆነ ቢረዱት መልካም ነው። ያለ ማወላወል ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም መቆም አክራሪ የሚያሰኝ ከሆነ እሰየው እንላለን።

በመጨረሻም የሚቀጥሉትን ሶስት አቋሞች በአንክሮ እንድትመለከቷቸው እንወዳለን፤

1. የቅንጅት ለዴሞክራሲና ለአንድነት ፓርቲ መሪ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ብቻ ናቸው። ቅንጅትም ይሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀውና የሚያምነው ይህንን ሐቅ ብቻ ነው። ከክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ላይ የመሪነቱን ሥልጣን በተንኮል እንነጥቃለን ተብሎ የተዘጋጀው መሣሪያ "ኮሌክቲቭ ሊደርሺፕ" እየተባለ የሚጠቀሙበት ፍሬ ከርስኪ ቃል ነው። ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እስኪለወጡ ድረስ ቅንጅት ያለው መሪ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ብቻ ናቸው። ከዚያ ውጭ ከቶውንም የማንቀበለው መሆኑን አጥብቀን እናሳስባለን።

2. እኛ እዚህ ትግል ውስጥ የገባነው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብለን እንጂ የጥቂት ሰዎችን የገንዘብና የሥልጣን ጥማት ለማርካት አይደለም። የቅንጅትን ትግልና ሕዝብ በደሙ መስዋዕትነት የከፈለበትን ለወያኔ ኢህአዴግ አሳልፎ የሚሰጥና የሚደራደር ግለሰብም ይሁን ቡድን በኛ ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

3. እኛም በቶሮንቶ የምንገኝ የቅንጅት ድጋፍ ጽህፈት ቤት አባላትና ደጋፊዎች ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የማይመሩት ወይም እሳቸው ይሁንታ ያልሰጡት የልዑካን ቡድን ወደ ቶሮንቶ፤ ካናዳ ቢመጣ የማንቀበል፣ የማናስተናግድና መምጣቱንም አጥብቀን የምንቃወም መሆኑን በአንክሮ እንገልጻለን።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

የቅንጅት ኢትዮጵያ የባሕልና የዕርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ
በካናዳ የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ አደራጅ ጽህፈት ቤት

ቶሮንቶ፤ ካናዳ
ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም

**ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ**
Kinijit Ethiopian Cultural and Relief Organization in Toronto
998 Bloor St West,, P.O.Box 10666, Toronto, ON  M6H - 1L8
**Tel./ Fax:  416 - 516 1244**

ነሐሴ 12 ቀን 1999 ዓ.ም

ለክብርት ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ
የቅንጅት ተ/ም/ሊቀመንበር
አዲስ አበባ፣
ኢትዮጵያ

ክብርት ሆይ፣

ከሁሉ አስቀድመን በፈጠራ ክስና በሀሰት ውንጀላ ተከሳችሁ በቃሊቲ እስር ቤት ከ18 ወራት በላይ ስትሰቃዩ ለቆያችሁት የቅንጅት አመራርና አባላት በሙሉ ያንን የመከራ፣ የግፍና የስቃይ እስር ቤት በአካልም በመንፈስም ተቋቁማችሁና ጸንታችሁ ለመፈታት በመብቃታችሁ በድጋሚ እንኳን ለዚህ አበቃችሁ:: እንኳን ደስ ያላችሁ ደስ ያለንም እንላለን::

የተጀመረውን የዲሞክራሲ ትግል ለመቀጠል፣ ሕዝብና መሪዎቹ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉበትን ትግል ከድል ለማድረስ ከእናንተው ጎን ቆመን የምንታገል መሆኑን አሁንም በድጋሚ እናረጋግጣለን::

ክብርት ሆይ፣

ለካናዳ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች (Chapters) "ጉዳዩ፣ የሥራ ጉብኝት ልዑካንና የዝግጅት ኮሚቴ አባላትን ስለማሳወቅ" በ 9/11/99 ዓ.ም በእርስዎ የተጻፈ ደብዳቤ በተዘዋዋሪ አግኝተን በካናዳ ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት የቦርድ ሥራ አስኪያጅ አካል ተወያይቶበታል:: ስለሆነም የቦርዱ የሥራ አስኪያጅ አካል ከዚህ የሚከተሉትን አስተያየቶችና ውሳኔዎች በአክብሮት ያቀርባል::

1ኛ/ የቅንጅት አመራር አባላት በአስከፊና የግፍ እስር ላይ በምትንገላቱበት ጊዜ ትግሉን ለማዳከም ይሯሯጡ ከነበሩ ግለሰቦች እጅ ገብቶ በተዘዋዋሪ መንገድ ለእኛ በመድረሱ ቅሬታ ተሰምቶናል:: ክቡርነትዎ ያውቀዋል ብለን በመገመት እስካሁን ስንሰራበት የነበረውን ሁናቴ ባጭሩ ለማስረዳት እንወዳለን::

ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት ማለትም በቶሮንቶ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪነት በተጨማሪ በካናዳ አዲስ ለሚቋቋሙ የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ዕውቅና መስጠት፣ ማደራጀትና ማስተባበር ኃላፊነት ተሰጥቶን ላለፉት ጥቂት ዓመታት ሥራውን ስናከናውን ቆይተናል::

አሁንም ይህንን በማድረግ ላይ ነን:: ይሁን እንጂ የእናንተን እስር ቤት መግባትና የጊዜውን ሁናቴ በመጠቀም ትግሉ ፈሩን እንዲስት ሲታገሉ የቆዩ ወገኖች ዛሬ የልዑካኑ ተቀባዮች ሆነው በመሰለፋቸው የተሰማንን መገረም ሳናስጨብጥዎት አናልፍም::

እንደ እውነቱ ከሆነ ማንኛውም መመሪያና ወይም መግለጫ ወደ እኛ ተልኮ ለማህበረሰባችን አባላት መረጃ እንድንሰጥበት ቢደረግ የድርጅቱን ሥራና ትግል ለተፈላጊው ውጤት ይደርሳል ብለን እናምናለን።

2ኛ/ ከላይ በአንደኛ ቁጥር እንደጠቀስነው በካናዳ የድጋፍ ድርጅቶችን በተመለከተ የተወሳሰበ ችግር መኖሩን ልናሳስብ እንወዳለን። ይህም በመሆኑ ወደ ካናዳ የሚመጣው የልዑካን ቡድን የቅንጅት የበላይ አመራርን ያቀፈ መሆን እንዳለበት፣ የልዑካኑም ቡድን ቁጥር ከሁለት መብለጥ እንደሌለበት አስቀድመን እናሳስባለን። በደብዳቤው ላይ እንደተጠቀሰው ወደ ካናዳ የሚመጣው የልዑካን ቡድን ከነሐሴ 20 ቀን 2007 ጀምሮ እንደሚመጡ ተጠቅሷል። የከፍተኛ አመራር ልዑካን ቡድን በቂ ዝግጅት ሳናደርግበት በችኮላ የሚላክበት ምክንያት አለ ብለን አናምንም። ስለሆነም፤ ከመስከረም አጋማሽ በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲሆን በአክብሮት እንጠይቃለን።

3ኛ/ ካናዳ ራሱን የቻለ አገር እንደመሆኑ መጠንና እኛም በካናዳ የድጋፍ ድርጅቶችን የማስተባበር ውክልና ኃላፊነት ተሰጥቶን ስንሰራ የቆየን በመሆናችን፤ በፖለቲካም ሆነ በማህበራዊ በኩል ያለውን ሁናቴ መከታተልና መፈጸም የሚገባን እኛ እንጂ ሌሎች ከካናዳ ውጭ የሚኖሩ የካናዳን ሁናቴና አሰራር የማያውቁ ግለሰቦች ይህን የተጣለባቸውን የማስተናገድ ኃላፊነት ሊወጡ እንደማይችሉ እንድታውቁት እንፈልጋለን።

4ኛ/ ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ ጽህፈት ቤት ለብዙ ጊዜ ቢሮ ከፍቶ ሕዝብ ሲያስተባብርና ሲያደራጅ፤ ከካናዳ መንግሥት ጋር ሲገናኝና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ሲሰራ የቆየ እንደመሆኑ መጠን በእርስዎ የተጻፈው ደብዳቤ በካናዳ ለሚገኙት በጠቅላላው ድርጅቶች እንጂ (በተዘዋዋሪ የደረሰን ደብዳቤ ግልባጭ ተያይዟል) ለአስተባባሪው ጽህፈት ቤት አለመሆኑ አስገርሞናል። ለወደፊቱም ማንኛውም የቅንጅት ፓርቲን የሚመለከት መመሪያ ወይም መግለጫ ሲወጣ ወይም እናንተ በካናዳ ስላለው ጉዳይ ማንኛውንም መረጃ ስትፈልጉ በእጃችን ስለሚገኝ ከላይ በተጠቀሰው አድራሻችን በቅድሚያ እንዲደርሰን በአክብሮት እናሳስባለን።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ፊርማ ያለው

ቢሹ ማሞ
ሊቀመንበር

<u>ግልባጭ፤</u>

ለክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል
<u>አዲስ አበባ</u>